

# ርብቃ

- አንድ ቀን አብርሃም በጣም አርጅቶ በነበረበት ወቅት በጣም የሚያምነውን አገልጋዩን ወደእርሱ ጠራው። እርሱና ሚስቱ ሣራ ለወለዱት ልጃቸው ለይስሐቅ ሄዶ ሚስት እንዲፈልግለት ያዘዋል። ይስሐቅ ልጁ ከከነአናውያን ሴቶች ሚስት እንዲያገባ አልፈለገም። ስለዚህም አገልጋዩ አብርሃም ወደተወለደበት ወደትውልድ አገሩ ሄዶ መልካም ሚስት እንዲፈልግለት ላከው።

- “እኔ የምመርጥለት ሴት ከእኔ ጋር ለመምጣት ፈቃደኛ ባትሆንስ?” ሲል አገልጋዩ አብርሃምን ጠየቀው። አብርሃምም እንዲህ አይነት ነገር ከገጠመው ከመሃላው ነፃ እንደሚሆን ነገረው። ስለዚህም አገልጋዩ ናሆር ወደምትባል ከተማ ሄደ። ለሚያገኛት ልጃገረድና ለቤተሰቧ የሚሆን አስር በሚያህሉ ግመሎች የተጫነ ስጦታም ይዟል። ወደአንድ የውሃ ጉድጓድ እንደደረሰም ግመሎቹ ተንበርክከው እንዲያርፉ አደረገ። ብዙ ልጃገረዶች ውሃ እየቀዱ በዚያ ነበሩ።

- እንዴት ነበር ለይስሐቅ የምትሆነውን ልጃገረድ መምረጥ የሚችለው? ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ፀለየ፣ “እባክሽን እንስራሽን አውርጂና ውሃ አጠጪኝ የምላት ልጃገረድ መልሳ ‘ጠጣ፤ ለግመሎችህም ውሃ አቀርብላቸዋለሁ’ የምትለኝ እርሷ አንተ ለባሪያህ ለይስሐቅ የመረጥክለት ሚስቱ ነች።”

- ልክ ይህን ፀሎት አድርሶ ከመጨረሱ አንዲት ቆንጆ ልጅ ወደ ጉድጓዱ መጣች። እንደፀለየውም ውሃ እንድታጠጣው ጠየቃት። እርሷም የተሸከመችውን እንስራ ከትከሻዋ አውርዳ የሚጠጣውን ውሃ በእጇ ሰጠችው። ቀጥላም ለግመሎቹ ውሃ ለማቅረብም ጥያቄ አቀረበችለት! በአፍንጫ የሚጠለቅ የወርቅ ጌጥ እና ሁለት የእጅ አምባሮች ሰጣት። የአብርሃም ዘመድ መሆኗንም አወቀ። ለይስሐቅ ሚስት የምትሆነውም እርሷ እንደሆነች አወቀ። እግዚአብሔር ፀሎቱን ሰምቶ መለሰ።

- ግመል እጅግ ብዙ ውሃ መጠጣት የሚችል እንስሳ ነው። ምናልባትም በጣም ትልቅ በሆነ ውሃ መያዣ ውስጥ ያለን ውሃ ጠጥቶ ላይረካ ይችላል። አገልጋዩ ደግሞ አስር ግመሎችን ይዞ ነው የመጣው። ለርብቃ ይህ ቀላል ስራ አልነበረም። ለአስር ግመሎች የሚሆን ውሃ ከጉድጓድ መቅዳት እንዴት ከባድ እንደሆነ አስቡ። ይህን ለማድረግ መፍቀዷ ምን ያህል መልካም ሴት እንደሆነች ያሳያል።

- ግመሎቹን በሙሉ ውሃ ካጠጣቻቸው በኋላ እየሮጠች ወደቤቷ ሄደች። ወንድሟ ላባ በአፍንጫዋ ላይ የነበረውን የወርቅ ቀለበትና የእጇን አምባር አየ። ከዚያም ወደጉድጓዱ ሄዶ አገልጋዩን ይዞት ወደቤት መጣ። አገልጓዩም የመጣበትን ምክንያት ለመንገር እጅግ ጓጉቶ ነበር። ታሪኩንም በሙሉ ነገራቸው። ቤተሰቡም በሙሉ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ተገነዘቡ። ርብቃም ወደከነአን እንድትሄድ ተስማሙ።

- ለርብቃም የወርቅና የብር ጌጣጌጦችን እንዲሁም ልብሶችን ሰጣት። ለቤተሰቦቿም ውድ ውድ ስጦታዎችን አበረከተላቸው። እነርሱም ርብቃ ለአስር ቀናት እንድትቆይ ፈልገው ነበር። አገልጋዩ ግን በቶሎ መሄድ እንዳለባቸው ነገራቸው። ርብቃንም ጠርተው ስለጉዳዩ ጠየቋት። እርሷም ለመሄድ ፈቃደኛ እንደሆነች ገለጠችላቸው። ከእርሷ ጋርም ሞግዚትና የሚያገለግሏት አገልጋዮችን ሰጧት።

- ወደ አብርሃም መኖሪያ መንደር አካባቢ ሲደርሱም አንድ ሰው በእርሻ መካከል ሲሄድ አየች። ከግመሏ ወረደችና ፈቷን ሸፍና የምታገባውን ባሏን ተገናኘችው። ይስሐቅም በጣም ወደዳት።

- በአንድ ወቅት ይስሐቅ በሚኖርበት አካባቢ ድርቅ ስለነበር ከሚኖርበት ከከነዓን ምድር ተነስቶ በፍልስጥኤማውያን ንጉስ በአቢሜሌክ ግዛት ለመኖር ተጓዘ።  ርብቃ እጅግ በጣም ቆንጆ ስለነበረች የአካባቢው ሰዎች እንዳይገድሉት ፈራ። ስለዚህ፣ "እህቴ ናት፣" አለ። ይህ ንግግር አዲስ ነው እንዴ? ከአመታት በፊት አባቱ አብርሃም አቢሜሌክን እንዲሁ ሳራ ሚስቱ ሳትሆን እህቱ እንደሆነች በመናገር ዋሽቷል። አቢሜሌክም በሁኔታው እጅግ ተቆጥቶ ለወገኖቹ ማንም ርብቃን እንዳይነካ አዘዘ።

- ይስሐቅና ርብቃ በጋብቻ ለሀያ ሁለት ዓመታት አብረው ቢቆዩም ገና ልጅ አልወለዱም ነበር። አሁን ግን አንድ ልጅ ብቻ ሳይሆን ሁለት መንታ ልጆች መወለድ ቻሉ! መጀመሪያ የተወለደው ልጅ በፀጉር የተሸፈነ ነበርና ኤሳው ብለው ጠሩት። ሁለተኛ የተወለደው ደግሞ ያዕቆብ ተብሎ ተጠራ። ትርጉሙም "ነጣቂ" ወይንም የሌላ የሆነውን በተንኮል የራሱ የሚያደርግ ማለት ነው።  ምንም እንኳን ኤሳው ታላቅ ቢሆንም ቤተሰብ ይመራ የነበረው ግን ያዕቆብ ነበር።

- ከጥቂት ዓመታት በኋላ  ያዕቆብ የቤተሰቡ መሪ እንዲሆን ርብቃ ትልቅ ሚና እንደተጫወተች እናያለን። ያዕቆብ በእናቱ እርዳታ አባቱን ይስሐቅን አታሎ ለኤሳው የተገባውን በረከት እርሱ ተቀበለ። ያዕቆብ በእናቱ በርብቃ እጅግ የሚወደድ ልጅ ነበር። እግዚአብሔር ትልቁ ትንሹን እንደሚያገለግለው ስለነገራት ምርጥ የሆነውን ሁሉ ለእርሱ ትመኝለት ነበር። በማጭበርበሩና በማታለሉ የተነሳ ኤሳው እጅግ ተቆጣ። በዚህ ምክንያትም ለመሸሽ ተገደደ። ርብቃም ያዕቆብን ወደ ወንድሟ ወደ ላባ ላከችው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ያዕቆብን አላየቻቸውም።

- ርብቃ መቼ እንደሞተች አናውቅም። ሆኖም አብርሃም ለሚስቱ ለሳራ በገዛው የቀብር ቦታ ላይ በሚገኘው ዋሻ ውስጥ እንደቀበራት እናውቃለን።

*ይህን የርብቃን ታሪክ በዘፍጥረት መፅሐፍ  ከምዕራፍ 24 እስከ ምዕራፍ 27 ድረስ ማንበብ ትችላላችሁ።*